N°47

# ቀስተደመና ሬድዮ

## (ከመኢሶን ስነጽሁፍ ዝግጅት ክፍል የቀረበ ትችት)

## ጤናማው ሂደት እንደነ አቶ መለስ መሸጋሸግ ነው

በህወሃት ውስጥ የተከሰተው የነጃዎች ትርምስ እየከፋና እየሰፋ ወደ ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ተዛምቶ መሄዱን አላቆመም። ይህ ትርምስ በዴሞክራሲያዊ ዘዴ፣ ልዩነቶች በህዝብ ፊት ነጻ ውይይት እየተካሄደባቸው የሚፈታበት ዘዴ ጠፍቶ አሁን በተያዘው «በሂሳብ ማወራረድ» መልኩ ከቀጠለ ውሎ ይደር እንጂ ለህዝባችን መትረፉና ሃገሪቱን ይህ ነው ወደማይባል ጥፋት ይዞ ሊነጉድ እንደሚችል እንዳለው ከወዲሁ መገመት አስቸጋሪ አይደለም።

አሁን በአለው ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ሃይሎችም ሆኑ ህብረተሰባችን ከዚህ ትርምስ ለሀገሪቱ በጎ ነገር እንዲወጣ ከመመኘት በስተቀር በነገሮች ላይ ምንም ጫና እንደሌላቸው ግልጽ ነው። የወያኔዎች ቅራኔ የተቀሰቀሰው እዛው ህወሃት ውስጥ በተከሰቱ ቅራኔዎች ነው። እየቀጠለ ያለውም እዛው ህወሃት ውስጥ በአለው የውስጥ የሃይል ሚዛን ነው። ግጭቱ ወደ ኢህአዴግ የተዛመተውና በመስፋፋትና በመክፋት ላይ ያለውም እዛው ኢህአዴግ ውስጥ ባሉ ቅራኔዎችና በአለው የውስጥ የሃይል ሚዛን ነው።

ጥያቄው እንግዲህ በዚህ መልክ ከቀጠለ ይህ ግጭት ወዴት ሊያመራ ይችላል የሚለው ብቻ አይደለም። የኛ ጭንቀት መሆን ያለበት ከዚህ ቀውስ ለዝች አገር በጎ ነገር እንዲወጣ የሚፈልጉ ሃይሎች ሁሉ ምን ማድረግ ይገባቸዋል የሚለው ጥያቄም ነው።

ግጭቱና ትርምሱ በዚህ ከቀጠለ ወዴት ሊያመራ ይችላል? ይህ ግጭት እንደተጀመረና እየሰፋም ሲሄድ ሁላችንም በጎ ነገር ነው ይቀጥል እንል ነበር። አንዳንድ አሽሟጣጮች ነገሩን ባጭሩ ለማስቀመጥ (እዚሁ ዝግጅታችን ላይ አንድ ካዲስ አበባ አደማጭ የላኩልን ደብዳቤ አርእስት እንዳደረጉት) «በህወሃት ውስጥ የተከሰተው መሰነጣጠቅ ለዘልአለም ይኑር» ሲሉም ይደመጡ ነበር። እውነትም ላይ ላዩን ሲታይ ነገሩ አስጎምጂ መልክ ነበረው። አቶ ስየ አቶ ቢተውና አቶ ሰለሞን ጢሞ ካቶ ኩማ ደመቅሳ፣ ከፕሬዜዳንት ነጋሶ ጊዳዳና ከነአቶ አባተ ኪሾ ባንድ ወገን እነአቶ መለስ ደግሞ ጄኔራል አባዱላ ገመዳን፣ አቶ አዲሱ ለገሰን፣ ዶክተር ካሱ ኢላላን ይዘው በሌላ ወገን በመቆማቸው በዚህ መልክ ብሄር ከብሄር ተደበላልቆ የሚካሄደው ትግል ከእንግዲህ በዚች አገር ያሉ የፖለቲካ ሃይሎች ህዝባችንን ከሚያስጨንቁትና ወጥረው ከያዙት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥያቄዎች አንጻር እገሌ ከእገሌ ሳይሉ በፖለቲካ አቋም ግራ፣ ቀኝ፣ ማህል፣ ሊበራል፣ ሶሻሊስት፣ ሶሻል ዴሞክራት እያሉ ሁሉም በብሄር አቀፍነት በሃገር ደረጃ ተሸጋሽገው በዚች አገር ጤናማ ለሆነ የፖለቲካ ህይወት በር የሚከፍት ሂደት ሆኖ እንዳየነው ግልጽ ነው። ከዚህ ያንጃዎች ትርምስ ሁላችንም ለሃገራችን የምንመኘው በጎ ነገር ሊወጣ የሚችለው ነገሮች ሁሉ በዚህ መልክ ቢቀጥሉ ነውና።

መገንዘብ ያለብን ግን አንድ ነገር አለ። አሁን ያለው የነገሮች አያያዝ ለእንዲህ አይነቱ ሂደት ዋስትና የሚሰጥ አያያዝ አይደለም። ዴሞክራሲ ታፍኖ በሚገኝበት ህብረተሰብ ውስጥ ያንጃዎቹ ትግል በዚያው በወያኔ/ኢህአዴግ ውስጥ የተለያዩ አንጃዎች ሂሳብ የሚያወራርዱበት ትግል ሆኗል። በዚህ ከቀጠለ ደግሞ ይህ ግጭት ዘልአለሙን ውስጣዊና «አህያ ከአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር» ብለን ችላ የምንለው ትግል ሆኖ አይቀጥልም። ቀስ በቀስ አስከፊ የሆነ የብሄር እንዲያውም ከዚያም አልፎ የጎጥና የንኡስ ጎጥ ገጽታ ይዞ ለህዝባችን የሚተርፍበት አደገኛ ሁኔታ እንዳለ መገንዘብና ይህንን ለመከላከል የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ በሱ አንጻር መራመድ ያስፈልጋል።

ግጭቶች ይህንን አስፈሪ መልክ የሚይዙባቸው ሁለት የተያያዙና የሚተጋገዙ ምክንያቶችም ከወዲሁ በግልጽ እየታዩ ነው። ባንድ በኩል ለጊዜው የበላይነት በመያዙ ብቻ ያጥፍቶ ጠፊ ፖለቲካ የሚከተለው የነአቶ መለስ ዜናዊ አቋም አለ። በፖለቲካ አቋማችሁ ከኔ ተለይታችኋል፣ ግን ደግሞ በህወሃትም ሆነ በኢህአዴግ ውስጥ ብዙሃኑን ማሳመን አልቻላችሁም፣ ማይኖሪቲ ናችሁ፣ከፈለጋችሁ በማይኖሪቲነት ቀጥሉ፣ ካልፈለጋችሁ ደግሞ ይህንኑ የተሸነፋችሁበትን አቋም ይዛችሁ ተሰባሰቡና ሌላ ድርጅት አቋቁማችሁ ታገሉ ብለው ቀደም ሲል እኛን «ነባር» ተቃዋሚዎቻቸውን ሲ

ሉን እንደነበረው «መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ» ብለው የመመረቅ ፖለቲካ አልመረጡም። ከዚህ ጤናማና ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ይልቅ የመረጡት ዘዴ ሙሰኝነትን እንደ ፖለቲካ ትግል መሳሪያ አድርገው መጠቀም ነው።

በዚህ ምክንያት ጸረ መለሱ አንጃ መፈናፈኛ አጥቷል። ቀሪው የኢህአዴግ አንጃ እርስ በእ ርሱ ተለጣጥፎ በአቶ መለስ ዜናዊ «መአከልነት» አንድ ወጥ ወደሆነ ጸረዴሞክራቲክ ህብረ ብሄር ድርጅትነት ሲያመራ ተቃዋሚው አንጃ እሱም በበኩሉ ተሰባስቦ ወደ ሌላ ህብረ ብሄር ድርጅትነት ለማምራት አላማውም፣ ራእዩም አቅሙም ያለው አይመስልም። ከዚህ ይልቅ ልክ እንአቶ መለስ « ሙሰኝነትን» የፖለቲካ ትግል መሳሪያ እንዳደረጉ ሁሉ በሙሰኝነት ተወንጅለሃል እየተባለ እጁን ከ ሚሰጠው ተቃዋሚ ውጭ ያለው ሃይል መሳሪያ ሲያደርግ የሚሞክረው «አስር አመት ሙሉ የትግ ሮችን የበላይነት ተቃውሜ ለብሄሬ በመቆሜ ይኸው ይህ ግፍ እየተፈጸመብኝ ነው» በሚል ፊሊጥ አሁን ማጣፊያው ሲያጥር አስር አመት ሙሉ ከነመለስ ጋር ገጥሞ ሲጨቁነውና ሲግጠው ወደ ነበ ረው ብሄሩ ፊቴን አዞርኩ ማለት እየሆነ ነው። ነገሩ ከእናቶ መለስ ጸረሙሰኝነት ዘመቻ ተብየ ነገ ር ይበልጥ ተአማኒነት አይኖረውም። የሚያጋልጠው አንድ ነገር ቢኖር እነዚህ የትላንት ግብረ አበ ሮች የዛሬ ተቃዋሚዎች ትላንት ረግጠው ለአስረገጡትና ዛሬ ደግሞ ድረስልን ለሚሉት ህዝባቸው የአላቸውን ንቀት ብቻ ነው። የሁለቱም አካሄድ ለሃገራችን ሰላምና ለኢትዮጵያ ህዝቦች ወንድማ ማችነት አደገኛ አካሄድ ነው እንላለን።

መፍትሄው ምንድን ነው? እኛ አጥብቀን መያዝ ያለብን ሁሉም ከብሄርና ከጎጥ በአሻገር በ ፖለቲካ አቋሙ በሃገር አቀፍ ደረጃ ይሸጋሸግ የሚል አቋም ነው። እነ አቶ መለስ አማራ፣ ኦሮሞ ፣ ትግራይ፣ ጉራጌ፣ ሃድያ፣ ከምባታ፣ ሲዳማ ሳይሉ በጸረ ዴሞክራሲ ህብረ ብሄር ድርጅት እየተ ቀናጁ ብቻ ሳይሆን አሁን የትግራይ መሰረታቸው እየሳሳ በመሄዱ የግዳቸውን የህወሃትን ያለፈውን የሞግዚትነት ሚና እያረገቡ ሁሉም ተለጣጣፊዎች በሁሉም የኢትየጵያ ህዝቦች ላይ ተጋግዘው ህብ ረብሄር የሆነ የጭቆና ቀንበር ለመጫን እየተሯሯጡ ነው። የህንን አደጋ ለመቋቋም ሁሉም በየብሄ ሩ መክተቱ የነአቶ መለስን ጨዋታ ማገዝ ብቻ ነው።

የህንን መፍትሄ ተቃዋሚው አንጃ እንዳይከተል ከእይታ ሌላ ችግሩ ምንድን ነው? ችግሩ ሌ ላ ምንም ነገር ሳይሆን በዚህ አንጃ ላይ ብቻ ሳይሆን ባገር የመጣው የዴሞክራሲ መጥፋት ችግር ነው። ዛሬ በነአቶ መለስ እየተገፉ «ዴሞክራሲ ጠፋ፣ የህግ የበላይነት ገደል ገባ፣ የየብሄራችን መ ብቶች ተጣሱ...» እያሉ የሚያማርሩት የተቃዋሚው አንጃ ደጋፊዎች ይህ ሁሉ የሆነው ላለፉት አ ስር አመት ከነአቶ መለስ ጋር መክረውና ዘክረው በዚህ ወይም በዚያ ብሄር ላይ ሳይሆን በጠቅላላ ው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተከሉት ስርአት ምክንያት እንደሆነ መረዳት ይኖርባቸዋል። ይህንን ከተረዱ ዘንዳ ደግሞ በዚህ አፋኝ ስርአት ውስጥ ለነሱ ብቻ የሚሆን ዴሞክራሲ ሊወርድ እንደማ ይችል ተገንዝበው ከሌሎች የሃገራችን ዴሞክራቶች ጋር ገጥመው ባንድነት መታገል ይኖርባቸዋል ።

ዞሮ ዞሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝቦች በሃገራችን የተረጋጋ የፖለቲካ ስርአት እንዲመሰረት የ ሚያስፈልጋቸው የሃይሎች በፖለቲካ አቋቋም መሸጋሸግ እውን ሊሆን የሚችለው በሰላምና በዴሞ ክራሲያዊ ዘዴ ህብረተሰባችን ወደ ሰላምና ወደዴሞክራሲ ሊሸጋገር የሚችልበት አንድ ዘዴ እነሱ ንም ሊያስተናግድ የሚችል ሁሉን አቀፍ አገራዊ ጉባኤ ተጠርቶ ኢተፖድሀና መላው ህብረተሰባች ን ባደረጉት ጥሪ መሰረት ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ሲደረግ ብቻ በመሆኑ ከዚህ አላማ አንጻር ግልጽ አቋቋም ይዘው ትግላቸውን ቢቀጥሉ ለነሱም ለሃገራችንም ከዚህ ያንጃዎች ትርምስ በጎ ነገር እን ዲወጣ የማይናቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

**ቀስተ ደመና ሬድዮ**

(17.08.01)

( **ነሃሴ** 8 **ቀን** 1993 **ዓ.ም.**)